# የመንፈስ ድክመት ለተናወጠው የዓለም ኢኮኖሚ ግሎባል ካፒታሊዝም መልስ ሊሆን አይችልም! ፕሮፌሰር ክላውስ ሸዋብ

## መግቢያ

በየዐመቱ በጥር ወር የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም በመባል የሚታወቀው ፣ ወደ ሁለት ሺህ አምስት መቶ የሚጠጉ ፣ በተለይም የካፒታሊስት አገር መሪዎች ፣ የዓለም አቀፍ ኢንስቲትቱሽን አለቃዎች ፣ በተለይም የትላልቅ የኢኮኖሚ ኢንስቲቱሽን ዋና ተወካዮች ፣ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎችና ፣ የባንክ ማኔጀሮች ፣ በዓለም አቀፍ የታወቁ ትችታዊ አመለካከት ያላቸው ኢኮኖሚስቶችና ፣ እንዲሁም አንዳንድ ትችታዊ አመለካከት ያላቸው ይሁንና ደግሞ የስብሰባውን ሂደት የማይረብሹ የሲቪክ ማህበራት ተጠሪዎች...ወዘተ. ዳቮስ የሚባለው ስዊዘርላንድ በሚገኘው በተራራ በተከበበ ከተማ ውስጥ ለአምስት ቀናት ያህል በመገናኘት ስለ ዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ፣ በተለያዩ ሴሽኖች በመከፋፈል በተለያዩ አርዕስቶች ላይ ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ ከጀመሩ ይኸው ከአርባ ዐመት በላይ ሆነው።

የመጀመሪያው ስብሰባ የተካሄደው በ1971 ዓ.ም ነበር። ሁኔታውን የሚያስታውስ ካለ እንዲሁ በጊዜው የዓለም ኢኮኖሚ ልዩ ዐይነት ቀውስና ክስተት የሚታይበት ዘመን ነበር። በ1944 ዓ.ም በብሪተንስ ውድስ የተደረሰበት ፣ ዶላርን ወደ ወርቅ የመለወጡ ስምምነት አሜሪካን በወሰደው ብቸኛ አቋም ይፈርሳል። የአሜሪካን የውጭ ሚዛን እየተናጋ ስለመጣና የውጭ ኢኮኖሚውም ተወዳዳሪነቱ በጃፓንና በጀርመን ስለተነጠቀ የወርቅ ክምችቱ ይቦረቦራል። በዚህም ምክንያት ብቸኛ አቋም በመወሰድ ከእንግዲህ ወዲያ ዶላርን በወርቅ እንደማይለውጥ ያስታውቃል። በ1973 ዓ.ም ደግሞ በቋሚ ከረንሲ (Fixed Exchange Rate) ምትክ በጠያቂና በአቅራቢ የሚወሰን ተለዋዋጭ ከረንሲ(Varaiable Exchange Rate) ተግባራዊ መሆን ይጀምራል። በተጨማሪም ለሰላሳ ዐመት ያህል ዕምርታን ያሳየው የካፒታሊስት አገሮች ኢኮኖሚ ወደ አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ ይገባል። የዋጋ ግሽበት መታየት ፣ የስራ አጥ ቁጥር መጨመር ፣ ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን እንዲያቀዘቅዙ የተገደዱበት ዘመንና ፣ በተለይም ደግሞ የጥሬ-ሀብት ጥያቄ መቀነስና ፣ በዚያውም የዓለም ንግድ መቀዝቀዝና የውጭ ንግድ ሚዛን መናጋት የሚታይበት ዘመን ነበር። ከዚህም ባሻገር ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ በምዕራብ አውሮፓና በአሜሪካን ሲሰራበት የነበረው በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በጥያቄ ውስጥ ይገባል። በጊዜው ለተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ የመንግስት ጣልቃ-ገብነት አንደኛው ምክንያት ሆኖ ይታመናል። ስለሆነም የኒዎ-ሊበራል አቀንቃኝ ኢኮኖሚስቶች አንገታቸውን ቀና በማድረግ የመንግስት ጣልቃ-ገብነት እንዲቆም ስትራቴጂ መቀየስ የጀመሩበትና ፣ በነፃ ገበያ ፖሊሲ አማካይነት ብቻ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መምጣት እንደሚቻልና ፣ በገበያው ውስጥ የሚታዩት መዛባቶች(Imbalances) ሊስተካከሉ እንደሚችሉ መስበክ ይጀምራሉ።

ከሰላሳ ዐመት ሙከራ በኋላ ይህ ዐይነቱ ልቅ የገበያ ኢኮኖሚ እንደተባለው በሁሉም መስክ ሚዛናዊ ዕድገትን አላመጣም። ፖሊሲው ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ወዲህ በካፒታሊስት አገሮችም ሆነ በሌሎች አገሮች በሀብታምና በተቀረው የህብረተሰብ ክፍል መሀከል ከፍተኛ የገቢ ክፍፍልና የሀብት ክምች ልዩነት መታየት ጀመረ። በብዙ አገሮች ጥቂቱ ሀብታም እየሆነ ሲመጣ ከአስር ሰዓት በላይ ላቡን እያንጠፈጠፈ የሚሰራ ሰራተኛ በደሞዙ ተዝናንቶ ሊኖር የማይችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። በዚህ ምክንያትና ፣ በተለይም ደግሞ በተጨባጩ የኢኮኖሚ መስክና በፊናንስ ካፒታል መሀከል በተፈጠረው ሰፊ ልዩነት የኒዎ-ሊበራል ልቅ የገበያ ኢኮኖሚ ጥያቄ ውስጥ መግባት ጀመረ። በ2007 ዓ.ም

የተከሰተው የፊናንስ ካፒታል ቀውስና ፣ ቀስ በቀስም ወደ ተጨባጩ ኢኮኖሚ(Real Economy) የተሻገረው አሳሳቢ ሁኔታ ካለመንግስት ጣልቃ-ገብነት ሊገታ እንደማይችል በራሳቸው በኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚስቶችም ሳይቀር ግንዛቤ ውስጥ ይገባል። በቀውሱ የተመቱ ባንኮችና የተቀረው የፊናንስ ኢንዱስትሪ የመንግስት ያለህ እያሉ መጮህ ይጀምራሉ።

እንደሚታወቀው በ2007 ዓ.ም አሜሪካን አገር ብዙ ቤተሰቦች በጣም ዝቅተኛ ገቢ እያላቸው ፣ ወይንም ምንም ገቢ ሳይኖራቸው ከባንክ በመበደር ቤት በመግዛት ወይንም በመስራት ለትልቁ የዓለም አቀፍ የፊናንስ ቀውስ ምክንያት የሆኑበት ወቅት ነበር። እዚህ ላይ ተበዳሪዎቹ ሳይሆኑ ለቀውሱ ዋናው ምክንያት የባንክን ወይም የብድርን ህግ በመጣስ ምንም አስተማማኝ ቋሚ ሀብትና ተከታታይ ገቢ ሳይኖራቸው በጭፍን ብድር ያበደሩት ባንኮችና ፣ በዚህ የቁማር ጨዋታ ውስጥ የተካፈሉት ልዩ ልዩ የፊናንስ ኢንዱስትሪዎች ናቸው። እዚህ ላይ አንዳንዶች አሜሪካን አገር የተከሰተው ከቤት መስራት ጋር የተያያዘው ቀውስና ፣ ዕዳን ለመክፈል አለመቻል እንዴት አድርጎ ለዓለም አቀፍ የፊናንስና የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሊሆን ይችላል? ብለው ሊጠይቁ ይችሉ ይሆናል። የአሜሪካን ባንኮችና የፊናንስ ኢንዱስትሪዎች ሪስኩን በተለይም ሌሎች የካፒታሊስት አገር ባንኮችም እንዲካፈሏቸው ዘዴ ይፈልጋሉ። ዕዳውን አንድ ላይ በማጠቃለልና ራሱን እንደገና በሴኩሪቲ ወይንም በመያዣ ወረቀት መልክ ለግዢ በማቅረብ የአየር ባየር ንግድ ጠባይ እንዲኖረው በማድረግ ብዙ ባንኮች እንዲሳተፉበት ያደርጋሉ። በዚህ ዐይነቱ የአየር ባየር ንግድ አማካይነት ሴኩሪቲው ወይም ወረቀቱ ከአንዱ እጅ ወደሌላው በመተላለፍ ለተወሰነ ጊዜ ዋጋው ከፍ ሲል ፣ በሌላ ወገን ግን የቤቶች ዋጋ ከተወሰነ ጊዜ ዕድገት በኋላ ዝቅ እያለ ይመጣል። በዝቅተኛ ወለድ የተገዙ ቤቶች ወለዱ ከፍ እያለ ሲሄድ ገዢ ማጣት ብቻ ሳይሆን ፣ ተበዳሪዎችም መክፍል የማይችሉበት ደረጃ ይደርሳሉ። የወለዱም ዋጋ በመጨመር ሁኔታውን ያባብሰዋል። ስለሆነም በብድር የገዙት ቤታቸውን የሚገዛቸው ያጣሉ። በዚህ ዐይነቱ የቁማር ጨዋታ ውስጥ የተሳተፉት ሌሎች የካፒታሊስት አገር ባንኮች ያፈሰሱትን ገንዘብ መልሰው ማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህም ምክንያት ብዙ ባንኮች ርስ በርሳቸው ለመበዳደርም ሆነ ለሌላው ለማበደር ፈሳሽ የገንዘብ እጥረት ይደርስባቸዋል። በተለይም በሪል ስቴት ውስጥ የተሳተፉት ባንኮች ወደመናጋት ይደርሳሉ። በዚህን ጊዜ ነው ባንኮችና ሌሎች የፊናንስ ኢንዱስትሪዎች መንግስቶቻቸውን የድረስልን ጩኸት ማሰማት የጀመሩትና ፣ መንግስታትም ባንኮችን ለማዳን የነፍስ ውጣ ግባ ማለት የጀመሩት። ከዚያን ጊዜ ወዲህ የመንግስት ጣልቃ-ገብነት አጠያያቂ ሊሆን አልቻለም።

ከአንድ ዐመት ተኩል ጀምሮ በተለይም ኦይሮ ዞንን ያዳረሰው የዕዳ ችግር ፣ በተለይም የግሪክ ፣ የጣሊያን ፣ የስፔንና የፖርቱጋል በዕዳ መተብተብ ይለፈፍ እንደነበረው ቀውሱ በገበያ ህግ ደንብ እንደማይፈታ አረጋግጧል። በተለይም ችግሩ በአንድ አገር ጫና ላይ የሚጣል መሆኑ ቀርቶ ጠቅላላውን የኦይሮ ዞንንም ሆነ ራሱን የአውሮፓውን አንድነትን ያናጋል በሚል ፍርሃት የተባበረ <እርምጃ> መወሰድ ከተጀመረ ይኸው ሰንበት ብሏል። ይሁንና ይህ ዐይነቱ በተለይም በጀርመን መሪነት ፣ በአውሮፓው አንድነትና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት(IMF) ተሳታፊነትና አማካይነት እንደ ግሪክ በመሳሰሉ ደካማ ኢኮኖሚዎች ላይ የሚደረገው ግፊት ሁኔታውን እያባባሰው እንደመጣም ግልጽ ነው።በግልጽ እንደሚታየው እስካሁን ድረስ የተወሰደው እርምጃ በመሰረቱ የግሪክ ኢኮኖሚ እንዲያገግምና ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያደርገው አይደለም። የባሰውን ኢኮኖሚውን በማድቀቅ ህልውናዋን በማጥፋት ላይ ይገኛል። ምክንያቱም የመንግስታትና የትላልቅ የዓለም ኢንስቲቱሽኖች ተሳትፎና ግፊት በኒዎ-ሊበራል ፖሊሲ ላይ የተመረኮዘ ስለሆነ በፍጹም ለዕድገት የሚያመች አይደለም ። በሌላ አነጋገር እነዚህ ጡንቻቸው ያበጡ እንደ ጀርመን የመሳሰሉ አገሮችና የዓለም አቀፍ ኢንስቲቱሽኖች ከግሪክ የሚፈልጉት አንድ ነገር ብቻ ነው። ዋናው ቁም ነገር የግሪክ ህዝብ በየጊዜው አንጀቱን ጠበቅ እያደረገ የሚያገኘውንም ሆነ መንግስት ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች የሚያወጣውን ወጪ በመቀነስና ስራተኛን በማባረር

ለአበዳሪ ባንኮች መክፈል አለበት።ወደ 15 ሺህ የሚጠጉ የመንግስት ሰራተኞች መባረር ሲኖርባቸው ፣ በግል ኩባንያ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ ደሞዙ ከ20-30% በመቶ መቀነስ አለበት። በተጨማሪም በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የህዝብ ሀብቶች መሸጥ አለባቸው። በዚህ መልክ ከዚህም ከዚያም የተሰበሰበው ገንዘብ ለአበዳሪ ባንኮች መተላለፍ አለበት። ይህ ብቻ ሳይበቃ ግሪክ በብሄራዊ ነፃነቷ ላይ ሙሉ ለሙሉ አዛዥ ልትሆን አይችልም። በተለይም ገቢዋንና ወጪዋን በአውሮፓው አንድነት በሚመደብ ሰው መቆጣጠር አለበት። ይህን የሰሙት የግሪክ ፖለቲኮኞች ፣ በተለይም የፊናንስ ምኒስተሩ የጀርመኖች ቅኘት ነው ብለው መልሰውታል። በታወቁት የጀርመን መንግስት አማካሪ የጠበብት ኢኮኖሚስቶች አባል በሆነት በፕሮፌሰር ቦፊንገር አገላለጽ እስካሁን ድረስ በግሪክ ላይ የተደረገው ግፊትና ተግባራዊ የሆነው የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ህግን የጣሰ ነው። ፖሊሲው ለጠቅላላው ኢኮኖሚ መፈናፈኛ በመስጠት ካለበት ቀውስ እንዲወጣ የሚያደርገው አይደለም።

በዚህ ሁኔታና ፣ ለሶስት ዐመታት ያህል ሞቅ ሞቅ ያለው የጀርመን የውስጥ ኢኮኖሚና የውጭ ንግድ እየቀዘቀዘ በመምጣቱና ፣ እንዲሁም በቻይና የሚታየው የዕድገት መቀዝቀዝና ከውጭ የሚገባውንም ዕቃ መቀነስ የዓለምን የኢኮኖሚ ሁኔታ ሊያናጋው ይችላል በሚባልበት ወቅት ነው የዘንድሮው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ስብሰባ የተካሄደው።

## የተዛባ የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ!

እንደሚታወቀው የዛሬ ሃያ ዐመት የሶሻሊስቱ ብሎክ ከፈራረሰ በኋላ ለዓለም ህዝብ ከእንግዲህ ወዲያ ዋናው ፍቱን መድሃኒትና ከችግራቸው አውጥቶ ደስተኛ የሚያደርጋቸው ግሎባላይዜሽንና ነፃ የገበያ ኢኮኖሚ ነው እየተባለ ነበር ይሰበክ የነበረው። ዓለም ከእንግዲህ ወዲያ እንደ አንድ መንደር የምትቆጠርበትና ፣ ሁሉም እንደችሎታው በዓለም ገበያ ውስጥ በመሳተፍ የብስኩቱ ተቋዳሽ መሆን የሚችልበት ዘመን መጣ ተብሎ ነበር የሚለፈፈው። የዓለም ገበያና የዓለም ኢኮኖሚ ሁሉንም እንደችሎታው የሚያሳትፍ ስለሆነ የሚጎዳ የለም። ይህንን ደግሞ ውጤታማ ለማድረግ ለነጻ ገበያ ማነቆ የሆኑ ነገሮች በሙሉ መገርሰስ አለባቸው። የገበያ ተዋንያን በሙሉ እንደፈለጉ የሚፈነጩባት ዓለም መፈጠር አለባት። ለዚህ ዐይነቱ የግሎባል ኢኮኖሚ ዕድገት ደግሞ በጊዜው መስፋፋት የጀመረው የሞባይል ስልክና ፣ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቆ የቪዲዮ ውይይት(Video Conference) ማድረግ ፣ በኢሜይል በተጨባጭ የሰዓት ልዩነት ግኑኝነት መፍጠር ፣ ከየትም ቦታ ሆኖ በሌፕቶፕ አማካይነት ግኑኝነት መፍጠርና ፣ በአውሮፕላንም ከቦታ ቦታ መሽከርከር በእርግጥም ዓለም ወደ አዲስ ሁኔታ ውስጥ የገባችና ወደ መንደርነትም የተለወጠችበት ዘመን ነበር የሚያስመስለው።

ስለሆነም ከምን ጊዜውም የበለጠ የነፃ ገበያ ተዋንያን የበላይነትን በመቀዳጀት ዓለምን ማሰስና መንግስታትን በማታለልም ሆነ በመስበክ የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ መወትወት የጀመሩበት ዘመን ነበር። እንደነ ዓለም የንግድ ድርጅት(WTO)የመሳሰሉት ደግሞ የድሮ ስማቸውን በመቀየርና አዳዲስ አጀንዳዎች በማካተት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከምን ጊዜውም የበለጠ ዕቃዎችና ካፒታል በመሽከርከርና ኢኮኖሚ ዕድገት በመታየት የዓለም ህዝብ ተጠቃሚ ይሆናል ብለው ይሰብኩ የጀመሩበት ዘመን ነው። በ2001 ዓ.ም የተጀመረው የዶኻው ዙር የሚባለው <ዕድገትን> ያካተተና ፣ በተለይም በእርሻ ድጎማ ቅነሳ ላይ ያተኮረ ክርክር ሞቅ ሞቅ ያለው ግሎባላይዜሽን መጧጧፍ ከጀመረ ወዲህ ነው። እንደ ህንድ ፣ ቻይናና ቬትናም የመሳሰሉት የንግድ ድርጅቱ አባል በመሆን ለዓለም ኢኮኖሚ ዕምርታም ሆነ ትርምስ የሰጡበት ዘመን ይኸው የግሎባላይዜሽን ወቅት ነው። ከቻይና በስተቀር ፣ አባዛኛዎቹ የድሮ የኮሙኒስት አገሮችና ራሺያም ጭምር መሉ በሙሉ በነፃ ገበያና በኒዎ-ሊበራል ፖሊሲ በመታለልም ሆነ በጭፍን ዕምነት ኢኮኖሚያቸውን ማዋቀር የጀመሩበት ወቅት ነው።

ስለሆነም ለነፃ ገበያ ኢኮኖሚ አመቺ ይሆናሉ የተባሉ ፖሊሲዎች በሙሉ ተግባራዊ መሆን ይጀምራሉ። በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበሩ ሀብቶችም ሆነ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ መስኮች ግልጽ ባልሆነ መንገድ ወደ ግል ሀብትነት ይዘዋወራሉ። የየአገሮች ካረንሲም ከዶላር ጋር በመነፃፀር ዝቅ እንዲል (Devaluation)ይደረጋል። የውጭ ከረንሲያቸውም እንደየገበያው ሁኔታ ከፍና ዝቅ የሚል ይሆናል። በኒዎ-ሊበራሎች ዕምነት አንድ አገር የወጭ ከረንሲዋን ዝቅ ስታደርግ ወደ ወጭ የምትልከውን ዕቃ ወይም የእርሻ ምርት በብዛት መሸጥ ትችላለች። በተጨማሪም መንግስት ለልዩ ልዩ መስኮች የሚሰጠውን ድጎማና በኢኮኖሚው ውስጥ የነበረውን ቀጥተኛ ተሳትፎ ማቆም አለበት። በዚህ መልክ ተግባራዊ የተደረጉት እርምጃዎች ሰባ ዐመት ያህል በመንግስት ዕቅድ አውጭነትና ቀጥተኛ ጣልቃ-ገብነት ሲተደዳር ለኖረ ህዝብ የቱን ያህል በህይወቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረው መገመቱ ከባድ አይደለም። በዚህ ዐይነቱ የምክር ሰጭነትና የግንባር ቀደምትነት ሚና እንደነ ፕሮፌሰር ጀፈሪ ሳክስ የመሳሰሉትና ፣ እንደተለመደው የዓለም የገንዘብ ድርጅት ተሰሚነታቸው ከፍ እያለ ይመጣል። በሌላ ወገን ግን እንደቻይና የመሳሰሉት አገሮች ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ በጥንቃቄ መውሰድ የጀመሩትን የገበያ ኢኮኖሚ ተግባራዊ በማድረግ ልዩ ዐይነት ዕድገት ያሳዩበት ሁኔታም እንዳለ ለብዙዎቻችን ግልጽ ነው። ይህም ማለት በአንድ በኩል በዓለም የገንዘብ ድርጅትና የታውቁ ኢኮኖሚስቶች በድሮው የኮሙኒስት አገሮች ውስጥ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የነፃ ገበያ ፖሊሲና ፣ በቻይና በጥንቃቄ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የገበያ ፖሊሲ በተለያየ ፍጥነት የሚጓዙ ነበሩ። የቻይና ኢኮኖሚ ቴክኖሎጂያዊ ምጥቀትን ሲያሳይና ፣ በተለይም በውጭ ንግዱ እየደለበ ሲመጣ ፣ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በታወቁት ኢኮኖሚስቶች የተመከሩት የቀድሞው የኮሙኒስት አገሮች መቀመቅ ውስጥ እንዲገቡ ይገደዳሉ።

የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ በብዙ የቀድሞው የኮሙኒስት አገሮች ተግባራዊ መሆን ከጀመረ በኋላ የተጠበቀውን ያህል ውጤት አላመጠም። በተለይም ራሺያ በዘጠናዎቹ ዐመታት የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የአሜሪካን ሰለባ በመሆን በዕዳ በመተብተብ ብሄራዊ ነፃነቷን ወደ ማጣት የተቃረበችበት ዘመን ነበር። በፕሬዚደንት ዬልሲን የሚመራው አዲሱ አስተዳደር የዓለምን የገበያ ኢኮኖሚ አወቃቀርና ፖለቲካ ሳይረዳ ሶቭየት-ህብረትን በማፈራረስና ራሽያን ብቻዋን በማስቀረት ወደ ሶስተኛው ዓለም ሁኔታ እንድትቀየር አመቺውን ሁኔታ ሁሉ በመፍጠር ከውስጥም ከውጭም በውጥረት ዓለም ውስጥ እንድትወድቅ ለማድረግ በቃ። በነፕሮፌሰር ጀፈሪ ሳክስ የሚመከረው አዲሱ የራሺያ ኤሊት ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው ፖሊሲ ራሺያን ማዳከሙ ብቻ ሳይሆን ምንም ሳይሰራ አዲስ የኦሊጋርኪ መደብ በመፈጠር ለጤናማ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለሚዛናዊ የሀብት ክፍፍል እንቅፋት ሆነ። በዚህም አማካይነት በዘጠነኛው ዓ.ም በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋት የጀመረው ግሎባል ካፒታሊዝም በየአገሮች ውስጥ ልዩ ዐይነት የሃይል አሰላለፍ በመፍጠር ፣ ጥቂቱን ሲያደልብ አብዛኛውን ደግሞ ወደ ድህነት ዓለም ገፈተረው። እንደተባለውና ለማሳመንም እንደተሞከረው ሁሉም እንደ አቅሙ የብስኩቱ ተቋዳሽ መሆን አልቻለም። በዚህ መልክ ግሎባል ካፒታሊዝምና ርዕዮተ-ዓለማዊ ፖሊሲው በየአገሮች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ከፍተኛ መዛባትን አስከተለ። የድሮ ኮሙኒስት አገሮች ውስጥ በሀብታምና በደሃ መሀከል ያለው ልዩነት መስፋቱ ብቻ ሳይሆን ፣ መንግስታት ራሳቸው በሙስና በመዝፈቅ ታሪካዊ ተልዕኮአቸውን ለመወጣት የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። ዛሬም ቢሆን ይህ ዐይነቱ በሙስና ውስጥ መዝፈቅ በተለይም በቡልጌሪያና በሩሜኒያ የተስፋፋ በመሆኑ ህዝቡ አለኝታ እንዲያጣ ሆኗል። ምስኪኑ ደሃ ህዝብና በተለይም ወጣቱ የዚህ ዐይነቱ የጎልበተኞች ኢኮኖሚ ሰለባ በመሆን ሰውነቱን እንዲሸጥ ተገዷል። ስንቱ ወጣት የድረግ ሰለባ ሆነ! ስንቶቹ ወጣት ሴቶችስ ህይወታቸው እንዲጠፋ ተደረጉ!!

በመቀጠልም ፣ በዘጠናዎቹ ዐመታት መጀመሪያ ላይ ሞቅ ሞቅ ማለት የጀመረው የብዙ አሺያ አገር ኢኮኖሚዎች ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ችግር ውስጥ መውደቅ ይጀምራል።

ከዓለም የፋይናንስ ወይም የካፒታል ገበያ ላይ ገንዘብ በመበደር ብዙ ቤቶች መስራት የጀመሩት እንደታይላንድ የመሳሰሉ አገሮች ካፒታሉ ወደ ወጭ ሲወጣ ኢኮኖሚያቸው ክፉኛ መዳከም ይጀምራል። በተለይም እንደነ ጆርጅ ሶሮን የመሳሰሉት የሄጅ ፈንድ ማኔጀሮች በብዙ የእሺያ አገሮች ላይ ያደረሱት ጉዳት በአንድ ወቅት ሀብታም የሆኑ ግለሰቦች ሀብታቸው በአሸዋ ቤት ላይ እንደተገነባ ቤት በቀላሉ እንደሚፈርስ ሁሉ የሱቅ በደረቴ ነጋዴዎች ይሆናሉ። እንደ አርጀንቲና የመሳሰሉት ደግሞ በዕዳ በመተብተብ ኢኮኖሚያቸው ክፉኛ መመታቱ ብቻ ሳይሆን ህዝቦቻቸውም የድህነትን ፅዋ እንዲቀምሱ ይገደዳሉ። በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ግፊት ተግባራዊ የሆኑ ኢኮኖሚ ፖሊስዎች በሙሉ ለብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ድህነትና ወደ ለማኝነት መገፍተር ምክንያት ይሆናሉ። መንግስታት አገሮቻቸውን ማስተዳደር ባለመቻላቸው የተነሳ ሙስናና ውንብድና በመስፋፋት ተራው ህዝብ ሙሉ በሙሉ ነፃነቱ መገፈፍ ይጀምራል። እንደነ ሜክሲኮ የመሳሰሉት አገሮች ደግሞ ከግማሽ በላይ በድረግ ካርቴሎች ቁጥጥር ስር በመውደቅ ህብረተሰቡ በፍርሃት ዓለም ውስጥ እንዲወድቅ ይደረጋል። በአወቅሁኝ ባይነት  በግሎባል ካፒታሊዝም ተዋናዮች በብዙ የላቲን አሜሪካ አገሮች ውስጥ ተግብራዊ የሆነው የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ወደ ውስጥ አዳዲስ ሀብት በመፍጠር የተስተካከለና ጤናማ ሁኔታ ከመፍጠር ይልቅ ህብረተሰብአዊ ምስቅልቅልነትና ድህነትን በመፍጠር የብዙ ሚሊዮንን ህዝቦች በሰላምና በብልጽግና የመኖር ህልም ተንጠልጥሎ እንዲቀር ያደርጋል።

ከዚህ ዐይነቱ የድቀት ኢኮኖሚ ፖሊሲ ትምህርት የቀሰሙት ብራዚልና አርጀንቲና የበለጠ ወደ ውስጥ ያተኮረ ፖሊሲ በመከተል ትንሽ እስትንፋስ ለማግኘት ይችላሉ። በተለይም በፕሬዚደንት ኪርሽነር የሚመራው የአርጀንቲና መንግስት ዕዳውን መሉ በሙሉ ልከፍል አልችልም በማለት ግትር ያለ አቋም በመውሰዱ ከውጭ ንግድ የሚገኘውን ገቢ ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች በማዋል አስገራሚ የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመሰክራል። በተለይም የቻይና የጥሬ-ሀብት ጥማትና እንደ ኃያል መንግስት ሆኖ መውጣት ለብራዚልና ለአርጀንቲና ፣ እንዲሁም ለተቀሩት የእሺያ አገሮች መፈናፈኛ መንገድ በመስጠቱ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ከፊናንስ ካፒታሊዝም ኩርኮማ በመላቀቅ ዛሬ ራሳቸውን ለመቻል በቅተዋል። በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና በካፒታሊስት አገሮች የሚመኩበትና በውሸት የሚደለሉበት ጊዜ አብቅቷል። ራሺያም ራሷን የቻለች ሆናለች። ይሁንና በቻይናም ሆነ በብራዚልና በአርጀንቲና ፣ እንዲሁም በራሺያ የሚታየው ሁኔታ ብዙ ነገሮች ይጎድሉታል። የተስተካከለ ዕድገት ጉዳይ ፣ በጥሬ-ሀብት ላይ ብቻ ከመመካት ይልቅ የበለጠ በማኑፋክቱር ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ መቀየስና የውስጡን ገበያ ማስፋፋት ፣ ህብረተሰብአዊ ሃላፊነት መሰማት(Social Awareness)፣ በተለይም ባህላዊ እንክብካቤ ማድረግ ፣ የአካባቢ ጉዳይና የጠቅላለው ህዝብ ደህንነት የሚታሰብባቸው ጉዳዮች ናቸው። እንደሚታወቀው ኢኮኖሚ ለኢኮኖሚ ተብሎ አይደለም የሚያድገው። የጠቅላላውን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻልና በማቴሪያልም ሆነ በመንፈስ የበለጠ እርግጠኝነት እንዲሰማው ለማድረግ ነው። ስለሆነም ህብረተሰብአዊ ትርምስ እንዳይፈጠር ከተፈለገ ኢኮኖሚው ከሌሎች ነገሮች ጋር ተቀነባብሮ እየተመዛዘነ መታቀድ አለበት።

ወደ አፍሪካ አገሮች ስንመጣ በተለይም በዘጠናዎቹ አጋማሽ ላይ ይታይ የነበረው የጥሬ-ሀብት ጥያቄ በአማካይ ሲታይ ስድስት በመቶ ለሚጠጋ የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት ሆኗል። ይሁንና ይህ ዐይነቱ በጥሬ-ሀብት ጥያቄ ላይ የተመረኮዘ የኢኮኖሚ ዕድገት በብዙ አገሮች ውስጥ የሚታየውን የተቅዋም ቀውስ(Structural Crises) ሊያስወግደው አልቻለም። በመሆኑም አድጓል የተባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ጥቂቶችን ከማደለብና ለምዕራብ አገሮችም ሆነ እንደቻይና ለመሰሳሰሉት አገሮች የፍጆታ ዕቃ ማራገፊያ ከመሆን በስተቀር  በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ ህዝቦች ላይ የኑሮ ለውጥ አላመጣም። በመጀመሪያ ደረጃ ፣ ብዙ የአፍሪካ መንግስታት መሪዎችና ፖሊሲ አውጭዎቻቸው ለህዝቦቻቸው ደንታ የላቸውም። በሌላ አነጋገር ብሄራዊ ስሜትና ብሄራዊ ኩራት ምን እንደሆነ የገባቸው አይመስሉም። በሁለተኛ ደረጃ ፣ በራሳቸው ከመተማመን ይልቅ እየመላለሱ የዓለም አቀፍ የገንዘብ

ድርጅት አጎብዳጅ በመሆን ለተስተካከለ የኢኮኖሚ ዕድገት የማያመች ፖሊሲ ይከተላሉ። ስለሆነም የጥሬ-ሀብትን እስከነንፍሱ ከመሸጥ በስተቀር ወደ መፌበረክነት በመለወጥ ዕውነተኛ ሀብት እንዲፈጠር ሊያደርጉ አልቻሉም። በሶስተኛ ደረጃ ፣ ከውጭ የሚገኘው ገንዘብ ለማሺኖች መግዣ ከመዋል ይልቅ ለቅንጦት ዕቃዎች መግዣ ነው የሚውለው። በአራተኛ ደረጃ ፣ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገር መሪዎች የየአገሮቻቸውን ሀብት የግላቸው አድርገው ነው የሚቆጥሩት እንጂ የህዝብ ሀብት እንደሆነ የተረዱ አይመስሉም። እንደፈለጉ ለውጭ ኢንቬስተሮች ለሚባሉት ፣ በመሰረቱ ዘራፊዎች የጥሬ-ሀብታቸውንና መሬታቸውን በመሸጥ ህዝቦቻቸውን ያራቁታሉ። ስለሆነም ፣ አገር ፣ ብሄራዊ-ነፃነት ፣ ህብረተሰብ ፣ ቤተሰብ መመስረትና ለመጭው ትውልድ መሰረት ያለው ቋሚ ነገር ጥሎ ማለፍና ፣ የህዝብን መብት ማክበር የመሳሰሉት ለአንድ ህብረተሰብ ተረጋግቶ መኖር እጅግ አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን የገባቸው አይመስልም። ሊገባቸውም የሚፈልጉ አይደሉም። አንዳንድ ለአፍሪካ ተቆርቋሪ የሆኑ የአውሮፓ ምሁሮች የሚጠይቁን ከኢትዮጵያ አንስቶ ያሉት የአፍሪካ መሪዎች በዕውነቱ መንፈስ አላቸው ወይ? እያሉን ነው። እንደ ዕውነቱ ከሆነ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ መንግስታትና ኤሊቱ ከላቲንና ከአሺያ አገሮች እስካሁን ድረስ ትምህርት ሊቀስሙ የቻሉ አይደሉም።

ያም ሆነ ከሃያ ዐመት በፊትም ሆነ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ግሎባል ካፒታሊዝምና ልቅ የነፃ ገበያ ነው ለሰው ልጅ መፍትሄ እያሉ ይሰብኩ የነበሩት ሁሉ ራሳቸውን እየጠየቁ ነው። ካፒታሊዝም ራሱ ለዓለም ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበረሰብአዊ ፣ ኢኮሎጂያዊና ባህላዊ ቀውስ ተጠያቂ ነው ብለው አፋቸውን ሞልተው መናገር ባይፈልጉም ፣ እየተወሳሰበ ለመጣው ችግር መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል እየጠቆሙ ነው። በተለይም የስብሰባው ዋና ሃላፊና አዘጋጅ ፕሮፌሰር ክላውስ ሽባብ ኤሊቱና ግሎባል ካፒታሊዝም መፍትሄ መስጠትም ሆነ መሆን እንደማይችሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ፣ በአሁኑ ወቅት በሶስተኛው ዓለም አገሮች ብቻ ሳይሆን በራሱ በአውሮፓ ውስጥም የሀብት ክፍፍል ልዩነት እየታየ ነው። በዓለም የሰራተኞች ድርጅት(ILO) ተጠንቶ በቀረበው መሰረት በአውሮፓ አገሮች ብቻ ወደ 45 ሚሊዮን የሚጠጋ የስራ አጥ አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገበ 957 ሚሊዮን የስራ አጥ አለ። በዚህ ላይ 1.1 ቢሊዮን የሚሆን በቀን ከሁለት ዶላር ብቻ በማግኘት በድህነት ዓለም ውስጥ የሚኖር ህዝብ አለ። ሌሎች ደግሞ እየሰሩም ለኑሮአቸው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ገዝተው ለመጠቀምም ሆነ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ለመላክ የማይችሉ አሉ። ከላይ የተዘረዘረውና ይህ ሁኔታ የዓለም ኢኮኖሚ በጤናማ ሁኔታ ላይ እንደማይገኝ ነው የሚያመለክቱት። ለብዙዎቹ ተሳታፊዎችም ሆነ ከውጭ ሆኖ ስብሰባውን ለሚከታተል የዓለም ሁኔታ በዚህ ዐይነት መልክ ወዴት ሊያመራ ይችላል? እያሉ ነው የሚጠይቁት።

## በስብሰባው ላይ ያልተነሳ ነጥብ! ሌላ ቦታ ለውይይት የቀረበ!

ስብሰባው ብዙ ተቃውሞዎች እንደደረሱበት ሁኔታውን የተከታተለ ሊገነዘብ ይችላል። በመጀመሪያ ደረጃ ስብሰባውን ከአደጋ የሚጠባበቁ በከፍተኛ መሳሪያ የታጠቁትን 5000 ወታደሮች ሳይፈሩ በአካባቢው ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉት የኦኩፓይ እንቅስቃሴዎች ያሰሙት የነበረው ፣ እንደዚህ ዐይነቱ ስብሰባና ተሳታፊዎች በህይወታችን ላይ መወሰን የለባቸውም የሚል ነው። እነዚህ ተቃዋሚዎች በእኛ አገር <ጨዋዎች> አባባል አናርኪስቶች ሳይሆኑ በከፍተኛ ዕውቀት የተካኑ ፕሮፌሰሮች ሁሉ ይገኙበታል። ከነዚህ ውስጥ የታውቁት የሶስዮሎጂና የህግ ምሁር ፣ እንዲሁም ከ2000-2008 ዓ.ም ድረስ የተባበሩት መንግስታት ምግብ የማግኘት መብት ተጠሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ጂአን ሲግለር ይገኙበታል። በሳቸውም አባባል እንደዚህ ዐይነቱ ስብሰባ ተሳታፊዎቹ እንዴት አድርገን ኃይላችንና ስልጣናችንን ማጠንከር እንችላለን ብለው የሚወያዩበት ሲርከስ እንጂ ለዓለም ህዝብ መፍትሄ ሊሰጡ እንደማይችሉ አስታውቀዋል። በእርግጥም እስከዛሬ ድረስ ካለግሎባል ካፒታሊዝምና ነፃ ገበያ መፍትሄ የለም ብለው ዓለምን ሲያራውጡ የከረሙት

ዋናው ዓላማቸው እንዴት አድርገን ግሎባል ካፒታሊዝምን እናድነዋለን ወይም ማን ያድንልናል ብለው እንጂ የሚከራከሩት የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት የሰው ልጅ በሙሉ በዚህች ምድር ላይ ከተፍጥሮ ጋር በመታረቅና ለስልጣኔ የሚያመች የዕድገት ፈለግ መቀየስ አለብን በማለት አይደለም የሚንቀሳቀሱት። ይህ ማለት ግን በመሀከላቸው ቅራኔ ወይም ሽኩቻ የለም ማለት አይደለም። ቀደም ብለው በማኔጀርነት ደረጃ ይሰሩ የነበሩ አንዳንድ ግለሰቦች ግሎባል ካፒታሊዝም ከሚያንቀዠቅዠን ይልቅ አዲስ ህይወት መጀመሩ ይሻላል ብለው ሙሉ በሙሉ ስራቸውን የለቀቁ አሉ። በስብሰባው ውስጥ ደግሞ የታውቁ የኢኮኖሚ ኢንስቲቱሽኖች ተጠሪዎች ራሳቸንን ከራሳችን ጋር የበለጠ ማገናኘት አለብን በማለት በተዘዋዋሪ እስከዛሬ ድረስ ይካሄድ የነበረው ስግብግብነት የመጨረሻ መጨረሻ ከቁጥጥር ውጭ እንደሚወጣና ሁሉም ተጠቂ እንደሚሆን አመልክተዋል።

በተቃራኒው ግን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ዋና ሃላፊ የሆኑት ወይዘሮ ላጋርድ ያሳሰባቸው ሁኔታ እየቀዘቀዘ የመጣው የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ የስራ አጥነት ቁጥር መጨመርና ፣ ወደፊት ደግሞ ብዙ አገሮች በራቸውን በመዝጋት ለዓለም ንግድ መቀዝቀዝ ሁኔታውን ያመቻቻሉ የሚለው ጉዳይ ነው። በሌላ አነጋገር ወይዘሮዋ የሚሉን በተዘዋዋሪ መንገድ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ቢያስፈልግም የግዴታ የነፃ ገበያ ሊታለፍ የማይችለው ፖሊሲ ነው። በሳቸው ዕምነት በነፃ ንግድ አማካይነት ብቻ ነው የማያቋርጥ ዕድገት ሊታይ የሚችለው። በሌላ ወገን ግን ሁሉም አገሮች የነፃ ንግድ እያሉ ርብርቦሽ የሚያደርጉ ከሆነ የቱን ያህል የጥሬ-ሀብት እንደሚወድምና የተፈጥሮም ሚዛን እንደሚናጋ ለመገንዘብ የፈለጉ አይመስልም። በአሁኑ ወቅት የጀርመን የፋይናንስ ምኒስተርና የክርስቲያን ዲሞክራቲክ ፓርቲ አባል የሆኑት ዶክተር ሾይብለ በማያቋርጥ ዕድገት ላይ ያለንን አስተሳሰብ መለወጥ አለብን ብለው አሳስበዋል። በተለይም በቁጥር የሚለካ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ በጀርመንም ሆነ በሌሎች የኢንዱስትሪ አገሮች በምሁራን ዘንድ የጦፈ ክርክር ይካሄዳል። የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄም የሰውን ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ሊያስታርቀው የሚችል ጥበብ የተሞላበት የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ዕድገት ፖሊሲ መንደፍ እንጂ ጭፍን የሆነ በነፃ ገበያ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ አይደለም። ይህንን የወይዘሮ ላጋርድን ንግግር ላዳመጠና ፣ በተለይም የአይሮን ችግርና የዕዳን ቀውስ አስታኮ ጀርመን በመንግስት የተደገፈ የዕድገት ኢኮኖሚ ፖሊሲ መከተል ስላለባት ጉዳይ ራሱ የዓለም የገንዘብ ድርጅት የቱን ያህል በቅራኔ ውስጥ እንደሚገኝ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ቀደም የዓለም የገንዘብ ድርጅት መንግስታት ባጀታቸውን ማስተካከል አለባቸው ፤ የመንግስታት ሚና መቀነስ አለበት ያላለውን ያህል አሁን ደግሞ እንደ ጀርመን የመሳሰሉ አገሮች የግዴታ ተሳትፎአቸውን ከፍ ማድረግ አለባቸው ይላሉ። በወዘሮ ላጋርድ ዕምነት የጀርመን ሰራተኛ ከሌሎች አውሮፓ አገሮች ጋር ሲወዳደር ዝቅ ያለ ደሞዝ ስለሚከፈለው ይህ ሁኔታ ለጀርመን ዕቃዎች በዓለም ገበያ ላይ በርካሽ ለመሸጥ አመቺ ሆኗል። ስለሆነም በአንድ በኩል የሰራተኛው ደሞዝ ከፍ ማለት ሲኖርበት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ተሳትፎ ማቀዝቀዝ የለበትም ይላሉ። እዚያው በዚያው ደግሞ የግሪክ መንግስት እስካሁን ድረስ በቁጠባ መልክ የወሰደው የባጀት የቅነሳ ፖሊሲ ስለማይበቃ የግዴታ ገፋቶ መሄድ አለበት ይሉናል። በሌላ አነጋገር ኢኮኖሚው የግዴታ መታነቅ አለበት። በደንብ ሳትመገብ እንደምትውል ላም የበለጠ ወተት ስጪ ብሎ በማለብ ጡቶቿን እንደማቁሰል ዐይነት በዚህ ዐይነቱ የኒዎ-ሊበራል የአንጀት አጥብቅ ፖሊሲ የግሪክ ኢኮኖሚ የባሰውኑ መራቆት አለበት። ያም ሆነ ይህ ከውጭ ሰላማዊ ሰልፍ በሚያደሩጉትና በተሳታፊው መሀከል ግልጽ ልዩነት የኖረውን ያህል ፣ ወደ ውስጥ ስብሰባው ላይ ደግሞ በተሳታፊዎቹ መሀከልም የወደፊቱን የነፃ ገበያ ፖሊሲና የግሎባል ካፒታሊዝምን ዕጣም ሆነ ችግር ፈቺነት ላይ ሙሉ ለሙሉ ስምምነት አለ ብሎ ለመናገር ያስቸግራል። በየሴሽኑ ከተሳተፉት አንዳንድ ኤክስፐርቶች የተሰጠው አስተያየት የወደፊቱ ሁኔታ አስተማማኝ እንዳልሆነ ነው የሚያመለክተው።

ይህ ዐይነቱ ስብሰባ ከመካሄዱ ሶስት ቀን በፊት በብዙ ሰዎች ዘንድ አትኩሮን ያላገኘ ቀደም ብሎ በዓለም ላይ የታወቁ ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ የሚጠጉ ኢኮኖሚስቶች

የተሳተፉበት የኢኮኖሚ ትምህርትን የወደፊት ዕጣ በሚመለከት ስብሰባ በጀርመን ምድር በፍራንክፈርት አማይን በሚባለው ከተማ ውስጥ ተካሂዷል። የሰሚናሩ ዋና አጀንዳ „*ኢኮኖሚን በአዲስ መልክ ማሰብ*“ የሚል ሲሆን በአብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የተደረሰበት መደምደሚያ እስካሁን ድረስ ሲሰራበትና ለትምህርት የተዘጋጀው የኢኮኖሚ ትምህርት ባለው ይዘቱ ሊቀጥል አይችልም የሚል ነው። ለምሳሌ የጀርመን ትልቁ ባንክ(Deutsche Bank) ዋና ኢኮኖሚስት ኢኮኖሚን እንደገና በአዲስ መልክ ማጠናቀር ያስፈልጋል ብለው ሲያሳስቡ ፣ በተለይም የንግድ ባንኮች ለትናንሽና ለማዕከለኛ ኢንዱስትሪዎችና እንዲሁም ለንግዱ መስክ በቂ የብድር ገንዘብ ማቅረብ ስለማይችሉ የማዕከላዊ ባንኮች ሚናውን ወደ መውሰድ ላይ ናቸው በማለት የሚታየውን የገንዘብ ፍሰት ችግር አመልክተዋል። በሌላ ወገን ግን እኚህ የጀርመን ባንክ ቺፍ ኢኮኖሚስት ያላነሱት ቁም ነገር አለ። በሚስተር ድራጊ የሚመራው የአውሮፓው ማዕከላዊ ባንክ ወደ 500 ቢሊዮን ኦይሮ የሚጠጋ ገንዘብ በዜሮ ወለድ ለንግድ ባንኮች አበድሯል። ባንኮቹ ግን አሁንም እንደወትሮው በገንዘቡ የአየር ባየር ንግዳቸውን አጧጧፉት እንጂ ለአነስተኛና ለመለስተኛ ኢንዱስትሪዎች አላበደሩም። የተዋቁት የኢኮኖሚ ጠበብቶች አባልና የጀርመን መንግስት አማካሪ የነበሩት ፕሮፌሰር ሩዩሩፕ የሚባሉት ደግሞ ከእንግዲህ ወዲያ የኢኮኖሚን ትምህርት የበለጠ በማቲማቲክ ሞዴል ማሽብረቁ ላለንበት ቀውስ መልስ ሊሆን አይችልም ብለዋል። ስለዚህም ይላሉ ፕሮፌሰሩ ፣ ወደ ኋላ አንድ እርምጃ መጓዙ የበለጠ ውጤታማ ነው በማለት እቅጩን ይናገራሉ። ኪል የሚገኘው ሌላው የጀርመን ከተማ ውስጥ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ምርምር ኢንስቲቱት ባልደረባ የሆኑት የኢኮኖሚ ምሁር ወይዘሮ ሊንዳ ደግሞ እስካሁን ድረስ የበለጠ በጥቃቅንና በረቀቁ ነገሮች ላይ በማትኮራችን አጠቃላዩን ሁኔታ እንድንስት ተገደናል በማለት የኢኮኖሚ ትምህርት ያለበትን ዋና ድክመት አመልክተዋል። ስለዚህም ይላሉ ሴትየዋ ፣ ኢኮኖሚን ከሌሎች የትምህርት መስኮች ጋር በማስታረቅና በማገናኘት ችግር ፈች እንዲሆን መዘጋጀት አለበት ይላሉ። ሌላው የአንድ ትልቅ የመኪና መለዋወጫና ልዩ ልዩ የቤት ዕቃዎችን የሚሰራ ዋና የኢኮኖሚ ጠበብትና ተካፋይ ደግሞ ፣ ኢኮኖሚስቶች ጤናማ አስተሳሰብ በማዳበር የኢኮኖሚክስ ትምህርት የሚታዩ ችግሮችን ሊፈታ እንዲችል ሆኖ መዘጋጀት አለበት ብለዋል። እንዲሁም በስብሰባው ላይ የተሳተፉት እንግሊዛዊቷ ኢኮኖሚስት ፕሮፌሰር ዲያን ኮይለ ማክሮ ኢኮኖሚ እስካሁን በሚሰራበት ይዘቱና መልኩ ሊቀጥል እንደማይችል አሳሰበዋል። የቀድሞው የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት(IMF) ዋና ኢኮኖሚስት የነበሩትና አሁን በሃርባርድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚያስተምሩት ፕሮፌሰር ኬነት ሮጎፍ እንደዚሁ እስካሁን ድረስ ለተከሰተው ዓለምአቀፋዊ የኢኮኖሚና የፊናንስ ቀውስ ተጠያቂው እስካሁን ስንሰራበት የነበረው መመሪያ ነው ብለው በራሳቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ትልቅ ክስ አቅርበዋል።

በስብሰባው ላይ የተካፈሉት በሙሉ በኢኮኖሚክስ ትምህርት ላይ ያላቸውን ቅሬታ በተለያየ መልክ ቢገልጹም እንዴት እዚህና እዚያ ላይ ለችግሩ ተጠያቂ ነው ብለው በዝርዝር አላመለከቱም። ከሌላው አማራጭ የኢኮኖሚ ዘርፍም ጋር በማወዳደር የችግሩን ዋና ምክንያት አልገለጹም። ይሁንና በሁሉም ዘንድ የነበረው ስምምነት ከታሪክ አንጻር በታዋቂ ምሁራን የተጻፉና ለትምህርት መመሪያ እንዳይሆኑ የተቀበሩ ከመቶና ከሁለት መቶ ዐመት በፊት የተዘጋጁ ለትምህርት እንዲያገለግሉ አሳስበዋል። በተለይም የዶግማ ታሪክ(Dogmengeschichte) የሚባሉት ፣ በታወቁት የጀርመን የጥንት ኢኮኖሚስቶች ፣ ሮሸ ፣ ፔሸ ፣ ሌክስ ፣ ሊስት እንዲሁም ሶስዮሎጂን ከኢኮኖሚክስ ጋር አያይዘው ትንተና ያቀርቡ የነበሩት እንደ ሽሞለርና ማክስ ቬበር ፣ የአውስትሪያው ሹምፔተርና የማርክስ ዳስ ካፒታል ፣ እንዲሁም አሜሪካዊው የኢንስቲቱሽናል ኢኮኖሚስት ምሁር ቶርስታይን ቬብለን ያዘጋጇቸው መጻህፍቶች ጠቃሚ እንደሆኑ አሳሰበዋል።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ምንድነው? የዓለም ኢኮኖሚ ትልቅ ፈተና ውስጥ እንደሚገኝ የሚጠቁም ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የብዙ ሰዎችን ጭንቀትና በቀላሉ መልስ ለመስጠት እንደማይቻል ያመልክታል። ይሁንና ግን የፈረንጅ ምሁራን ዝምብለው እንደማይተኙና

ለሚገጥሟቸው አዳዲስ ችግሮች መፍትሄ ለመፍጠር እንደሚጥሩ ነው። እንዲያው እስካሁን ስንሰራበት ከነበረው መመሪያ ወይም ትምህርት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም ብለው ዝምብለው ወደፊት ለመሄድ የሚፈልጉ አይደሉም። በሌላ ወገን ግን ለምን ከሌሎች ተቃዋሚዎች የሚነሳውን ትችት እስካሁን ድረስ እንዳልሰሙ ሆነው መቀጠል ተገደዱ የሚለው ጥያቄ የሚያስነሳባቸው ነው። ያም ሆነ ይህ በዚህ ዐይነቱ ትችታዊ አመለካከታችሁ ግሩብት እንላለን። ከስህተት መማር ማንኛውም የሰው ልጅ መከተል ያለበት ፊለግ ነው ስለሆነ አሁን በኢኮኖሚ ላይ የተነሳው ጥያቄና ክርክር ለኛም ሳይጠቅመን የሚቀር አይመስለኝም። የአስተሳሰብ አድማሳችንን ያሰፋዋል የሚል ዕምነት አለኝ። ሁላችንም የዚህች ምድር ባላቤቶችና አካል እንደመሆናችን መጠን ለብቻችን ከተማርነው ውጭ ሌላ አማራጭ የለም ብለን ልንሸመጥጥ አንችልም።

## ዋናው ጥያቄ የግሎባል ካፒታሊዝም ወይም የቲዎሪ ችግር!

በዳቮሱ የሲውዘርላንድ ስብሰባ ላይም ሆነ የፍራንክፈርቱ ላይ መነሳት ያለባቸው መሰረተ-ሃሳቦች አልተነሱም። ይኸውም የዛሬው ካፒታሊዝም ከሁለትና ከሶስት መቶ ዐመት በፊት እንደነበረው ዐይነት አይደለም። ከተራ የአገር ውስጥ ውድድር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በትላልቅ መልቲ-ናሽናል ኩባንያዎች መሀከል የጦፈ ትግል ይካሄዳል። በዚህ ዐይነቱ ውድድር ውስጥ የመንግስታት ሚና ዐይነተኛ ሚና በመጫወት ጥቅማችንን እናስጠብቃለን በሚል በሰው አገር በልዩ ልዩ ዘዴዎች ጣልቃ የሚገቡበት ሁኔታ ተመቻችቷል።ፖለቲካዊ፣ ርዕዮተዓለማዊና ኢኮኖሚያዊ ግፊቶች ብዙ ደካማ አገሮችን አላፈናፍን ብሏል። በተጨማሪም የብዙ የካፒታሊስት አገር ኢኮኖሚዎች በከፊተኛ ደረጃ ሚሊታራይዝድ ሆኗል። ይህ እንደኛው ሲሆን፣ የካፒታሊዝም ዐይነተኛ የምርት ክንውን የሚካሄደው በመጀመሪያ ደረጃ የሰውን ልጅ ፍላጎት ለማሟላት አይደለም። ማንኛውም ግለሰብ በገበያ አማካይነት ብቻ ነው ፍላጎቱን ማሟላት የሚችለው። ለዚህ ደግሞ የስራ መስክና በቂ ደሞዝ ማግኘት አለበት። በሌላ አነጋገር የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በማግለል ፕሪንስፕል(Exclusion) ነው የሚሰራው። በሶስተኛ ደረጃ፣ ስራ ያለው እንኳ ከምግብና ከቤት እንዲሁም ከልብስ ውጭ ያለውን ተጨማሪ ፍላጎት በደሞዙ ብቻ ሊያሟላ አይችልም። መኪናና ሌሎች የረዥም ዕድሜ ያላቸውን ምርቶች ለመግዛት የግዴታ ብድር ውስጥ መግባት አለበት። በአሜሪካም ሆነ በብዙ የካፒታሊስት አገሮች ኢኮኖሚው ካለብድር መንቀሳቀስ አይችልም። በሌላ አነጋገር ብድር የኢኮኖሚው ዋና አንቀሳቃሽ ሃይል ነው ማለት ነው። በአራተኛ ደረጃ፣ የገቢና የሀብት ክፍፍል እየሰፋ የመጣ ነው። በተለይም ኢንቬስትሜንት ባንኮች ወይም በጀርመን ፖለቲከኞች አነጋገር አንበጣዎች ቤት በመግዛት በተለይም በትላልቅ ከተማዎች ውስጥ ተራው ሰውም ሆነ ትንሽ ሻል ያለ ደሞዝ የሚያገኝ እንዳይኖር እያደረጉት ነው። ስለሆነም ባለፉት ሰላሳ ዐመታት በብዙ የካፒታሊስት አገሮች ከፍተኛ የሀብት ሽግሽግና ቀስ በቀስ እያለ ሀብረተሰቡን የሚሰረስር ድህነት እየታየ ነው። በተጨማሪም የፋይናንስ ካፒታል ከህዝቡ በተለያየ መልክ፣ ለምሳሌ የማያስፈልጉ ኢንሹራንሶች፣ መከፈል ካለበት መደባዊ የጡረታ አበል በተጨማሪ በካፒታል ማርኬት ላይ የሚሽከረከር የጡረታ አበልና ሌሎች የፋይናንስ ፕሮዳክቶች በመፍጠር ከሰፊው ህዝብ ገንዘብ በመንጠቅ የራሱን ሀብት እንዳይፈጥር እንቅፋት ሆኗል። በዚህ መልክ በህግ በተፈቀደና በረቀቀ ዘረፋ በብዙ ሚሊዮን የሚጠጉ ህዝቦች እንዲራቆጡ ሆነዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ከፍተኛ የሀብት ዘረፋ እየተካሄደ ነው። በተለይም የመሬት መሸጥ(Landgrabbing)፣ ስትራቴጂክ ጥሬ-ሀብቶችን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የአካባቢ ቀውስ በመፍጠር የሰውን ጤንነት መረበሽ፣ በሶስተኛው ዓለም አገሮች ገበያ ላይ የሚጣሉት በቀላሉ ሪሳይክል ሊደረጉ የማይችሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን ፍዳ ውስጥ ከተዋቸዋል። ከዚህ ባሻገር ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገር ህዝቦች በምግብ ራሳቸውን እንዳይችሉ የተለያየ ተንኮል እየተሰራባቸውና፣ በገበያቸው ላይ ርካሽ በቆሎና ስንዴ በመፍሰሱ ብዙ ገበሬዎች ወደ ድህነት ዓለም እየተገፈተሩ ነው። በዚያውም መጠን የእርሻ ባህልና ሀብረተሰብአዊ ግኑኝነቶች እየፈራረሱ ነው። በግሎባል

ካፒታሊዝም ግፊትና ከመንግስታት ጋር በመቆላለፍ እንደ ኢትዮጵያ የመሳሰሉ አገሮች ደግሞ ጤናማና ዘላቂነት ያለው ፣ እንዲሁም የረጋ ማህበረሰብና ህብረተሰብ እንዳይገነቡ ታግደዋል። ባጭሩ የዓለም ማህበረሰብ ግሎባል ካፒታሊዝም እንደፈለገው የሚጎትተው ወደመሆን ተሸጋግሯል።

ስለሆነም በተለይም ባላፉት 60 ዐመታት ዓለምን የሚቆጣጠረው ግሎባል ካፒታሊዝም ራሱ ለስልጣኔ ጠንቅ ሆኗል።እያንዳንዱ አገር ያለውን የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ኃይል በስነስርዓት በመጠቀም የዕውነተኛ ስልጣኔ ባለቤት እንዳይሆን አግዶታል። በተለይም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ የተቋቋሙት እንደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የመሳሰሉት ብዙ የሶስተኛውን ዓለም አገር ኤሊቶች በማሳሳት የየአገሮችን ዕድገት አዛንፈዋል። ያላቸውን ምሁራዊ ድክመትና በሰፊው ማሰብ አለመቻል በመረዳትና ተቀጥያቸው በማድረግ በተጨባጭ በየአገሮች ውስጥ ድህነትና መዝረክረክ እንዲስፋፋ አድርገዋል። ለህዝብ አለመረጋጋትና ለጦርነት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ፈጥረዋል። እንደሚታወቀው አንድ ህዝብ ከተማረ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት ከሆነና ፣ በዚያውም የመፍጠር ኃይሉ ከፍ ካለ በሰላም የመኖር ፍላጎቱ እየጨመረ ይሄዳል። እነዚህንና ሌሎቸ መሰረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ በሁለቱም ስብሰባዎች ላይ ውይይት አለተካሄደባቸውም። ወደፊትም ለውይይት አጀንዳ ሆነው ይቀርባሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው። ስለዚህም በቲዎሪ ደረጃ መወያየቱና ለራሳቸን መፍትሄ መፈለጉ ይመለከተናል በምንለው በራሳችን ትከሻ ላይ የሚወድቅ ይሆናል ማለት ነው። መልካም ንባብ!

**ፈቃዱ በቀለ**

fekadubekele@gmx.de